# በህወሃት ሤራ የተከናወነው የሱዳን ወረራ በኦታዋ ሰላማዊ ሰልፍ ተወገዘ




የካናዳ ዋና ከተማ በሆነችው በኦታዋ ከተለያዩ ከተሞች የተሰባሰቡ ኢትዮጵያዉያን በምዕራብ ኢትዮጵያ በሱዳን ወታደሮች የተደረገዉን ድንበር ዘለል ወረራ በመቃወም ባለፈዉ ዓርብ፤ ግንቦት 15፣ 2000 ዓ.ም ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዉ ዉለዋል። ይህ ከቶሮንቶና ሞንትርያል ከተሞች በመጡና በኦታዋ ኗሪ በሆኑት ኢትዮጵያዉያን ተሣትፎ የተደረገዉ ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የሱዳን ወታደሮች ድንበር አቋርጠዉ ላደረጉት ጥቃት ዋነኛ ምክንያትና ተባባሪ የሆነዉን የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ሤራም አጥብቀዉ አውግዘዋል። ለሃገር ሉዓላዊነት ደንታ የሌለዉ የመለስ ዜናዊ አምባገነን ቡድን ዛሬም እንደገና ሃገሪቱን ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅሙ ሲል ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱ ታሪክ ምህረት ሊያደርግለት የማይችል ክህደት መሆኑን የሰላማዊ ሰልፈኛዉ በቁጭት ባሰማዉና በጽሁፍም በያዘዉ መፈክሩ ገልጿል።

በሱዳን ኤምባሲ በር ላይ፤ የአካባቢዉ ነዋሪ እስኪገረምና የከተማዉ ፖሊሶችም መጥተዉ መስተንግዶ እስኪሰጡ ድረስ፤ ሠፈሩን ያናወጠዉ ሰልፈኛ “በአጼ ዮሐንስ ደምና በጀግኖች አባቶቻችን አጥንት የተጠበቀዉ ድንበራችን ለሱዳን አይሸጥም፣ ሱዳን ወረራዉን በማቆም ባስቸኳይ ይዉጣ፣ ተጠልፈዉ የተወሰዱ ኢትዮጵያዉያን ገበሬዎች ባስቸኳይ ይፈቱ....ወዘተ፤ የሚሉ መፈክሮችን አሰምቷል።




ከዚያም ሠልፉን ባስተባበረው ወገን በተጻፈና ለካናዳ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ተጽፎ በተሰጠ ደብዳቤም፣ በ1997 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ በድምጹ አምባገነናዊ አገዛዙን እንደሻረና ይህንን ውሳኔ-ህዝብ ያልተቀበለው የመለሰ መንግሥት ግን ምርጫውን ያሸነፉ ተመራጮችን እስር ቤት አጉሮ በጠመንጃ ኃይል ሥልጣኑን እንደያዘ መቀጠሉንና ይህም ከሃዲ መንግሥት ሥልጣኑን ለማቆየት እስከረዳዉ ድረስ የሃገሪቱ ዳር ድንበር መደፈር አንዳችም ደንታ የማይሰጠው መሆኑን አስረድተዋል። ይህ ኃላፊነት የጎደለው ጎጠኛ መንግሥትም አስተዳድራታለሁ የሚላትን አገር ዳር ድንበር አስደፍሮና የኢትዮጵያን መሬት ገምሶ ለሱዳን እንዲቸር ካበቁት ምክንያቶች አንዱ የሱዳን መንግሥት በምላሹ ኢትዮጵያዉያን የፖለቲካ ጥገኞችን መብት እንዲነፍግ፤ ተቃዋሚ የሚባሉትን ወገኖችም ካሁን በፊት እንዳደረገዉ በጥብቅ እንዲቆጣጠርለትና ለመለስም አሳልፎ እንዲሰጥ ታስቦ የተደረገ እንደሆነ አጽንዖት በመስጠት ይሄው ደብዳቤ ይገልጻል።

በመጨረሻም፤ የካናዳዉ ጠቅላይ ሚኒስትር ያላቸዉን ዲፕሎማሲያዊ ኃይል በመጠቀም የሱዳን ወታደሮች ከኢትዮጵያ ምድር ባስቸኳይ ለቀዉ እንዲወጡ፤ ታፍነዉ የተወሰዱት ኢትዮጵያዉያን እንዲፈቱ እንዲያደርጉና በኢትዮጵያዉያን ገበሬዎች ላይ የደረሰውንና እየደረሰ ያለዉን ግድያ፣ እንግልትና የሰብዓዊ መብት ረገጣም የሚከታተልና የሚዘግብ የመልዕክተኛ ቡድን ወደ ሥፍራው እንዲልኩ ጠይቀዋል።

ይህንንም ሰላማዊ ሠልፍ ቮይስ ኦፍ አሜሪካ የአማርኛው ክፍልና የህብረት ራዲዮ ተከታትለው ለህዝብ መዘገባቸው ታውቋል።

**የሰላማዊ ሠልፉ አስተባባሪ ኮሚቴ**